ዴሞክራሲያ
የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

# ሀገራችን መስቀለኛ መንገድ ላይ ነች፣ መፍትሄው በየት?

**ቅጽ 47፣ ቁጥር 1** **ሚያዝያ 2011 ዓ. ም**

ባለፉት 44 ዓመታት፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ በአንድ በኩል“የመደብ ትግል” በሌላ በኩል ደግሞ “የብሄረሰብ የነፃነት ትግል” እየተባለ ቆይቶ፣ ከ28 ዓመታት በፊት ሥልጣን ላይ የወጣው ህወሓት-መራሹ ኃይል በብሄረሰብ መብቶች መከበር ስም በአገሪቱ ውስጥ የመለያየትን መርዘኛ ሥርዓት መሠረተ። በሃያ ስምንቱ ዓመታት ውስጥ ጎሰኝነት፣ ጎጠኝነትና ከባቢያዊነት፣ በአጠቃላይ አንድነትን የሚያላሉ፣ ልዩነቶችን የሚያገዝፉ ተግባራት እየተከናወኑ፣ የአንዱ ብሄረሰብ አባል የሌላውን ብሄረሰብ አባል እንደ ባለመብት የሀገሩ ዜጋና የብሄራዊ አንድነቱ አካል ሳይሆን እንደባላንጣ አድርጎ እንዲመለከተው ተደርጓል።

በ1960ዎቹ በተጀመሩት ሀገርአቀፍ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥም፣ ከፖለቲካ ልምድ ማጣትና ከህቡዓዊ አደረጃጀት ጋር በተያያዘ ምክንያት ውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲዳብር አልሆነም። የአገዛዙን አፋኝነት መቋቋም ያልተቻለበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ ከብሄርተኛ ድርጅቶችም ጋር ግንባር መፍጠር አልተቻለም። እንዲያውም ብሄርተኞቹ ድርጅቶች ሀገርአቀፍ ድርጅቶችን በጋራ የማጥቃት ሁኔታ የተከሰተበት ወቅት ነበር።

በ1983 ዓ. ም. የጎሣ ፖለቲካ አራማጆች ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ለዓመታት ሲያጎለብቱት የቆዩትን የጎሰኝነት ፖሊሲ በአገሪቱ ላይ በሕገ-መንግሥት መልክ በመጫን የዛሬውን ጽልመት ያስከተለውን አካሄዳቸውን ጀመሩ። ጽልመቱ የተጀመረው በ1983 ዓ. ም. በተደረገው የሽግግር ጉባዔ ላይ ሀገርአቀፍ ድርጅቶች የነበሩትን፣ ኢዴህን፣ ኢሕአፓና መኢሶንን እንዳይሳተፉ በማድረግ ነበር። የአማራው ብሄረሰብም በሽግግር ጉባዔው ላይ እንዳይወከል ማድረጋቸው የጎሣ ፖለቲከኞችን የጥላቻ ፖለቲካ ይፋ ያወጣም ነበር።

የኤርትራን ነፃነት ማወቅና መቀበሉ ሀገራችንን የባህር በር ያሳጣ ከመሆኑም አልፎ ለኤርትራ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያዳላ መሆኑ የታየበት ነበር። የህወሓትና የሻዕቢያ የፖለቲካ ጫጉላ በከፋ ጠርነት ሲቋጭ፣ በርካታ የሕይወት መስዋዕትነት ያስከፈለ፣ በርካቶችን የአካል ጉዳተኞች ያደረገ፣ ከፍተኛ የንብረት ውድመትን ያስከተለ፣ በርካቶችን ያፈናቀለና ዘግናኝ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትንም ያስከተለ ነበር።

በጎሣና በቋንቋ ላይ የተመሠረተው ፌደራሊዝም፣ ሃገራዊ ማንነትን አጥፍቶ በጠባብ የብሄረሰብ ማንነት በተቀነበበው አስተዳደር፣ ክልሎች ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ሳይሆኑ በአብዮታዊ ዴሞክራሲና በ"ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት" ተወጥረው ከላይ ወደታች የሚወርድላቸውን መመሪያ የሚያስፈጽሙ መሣሪያዎች እንዲሆኑ ተደርጎ የተዋቀረ “ፌደራሊዝም” ነበር የተመሠረተው። ሥርዓቱ፣ በጠባብነት አስተሳሰብ የተመሠረቱ ድርጅቶች ቀደም ሲል በነበራቸው የዘረኝነትና የጥላቻ ሥነልቡና መሠረት በአገሪቱ ውስጥ የበለጠው ድርሻ ለኔ ይገባኛል የሚለውን ጥያቄቸውን እያከረሩ እንዲመጡ አድርጓል። ለምሳሌ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር መሪ በ1983 ዓ. ም ሲናገሩ “የኦሮሞ ልጆች የሰፈሩበት መሬት ሁሉ የኦሮሞ ልጆች መሬት ነው” ሲሉ የተደመጡ ሲሆን፣ የይገባኛል ጥያቄው እያደር እየጨመረ መጥቶ ሌሎች ብሄረሰቦች የሰፈሩባቸውን መሬቶች ለመውሰድ በተደረገው እንቅስቃሴ በርካቶችን የማፈናቀል ሥራ ተከስቷል። ዘረኝነት ከጽንፍ ጽንፍ አቢይ ጉዳይ ሆኖ ሲናኝ ኢትዮጵያዊነት ግን ሆን ተብሎ እንዲቀጭጭ ተደረገ። ከዚህም በላይ ሦስት አሥርተ-ዓመታት ለተጠጋ ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ የተጋተው የጎሣ ፖለቲካ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የጋራ ታሪክ እንደሌላት፣ አሻራዋም በዚህች ዓለም ላይ እንዳይቀር የታሪክን ትምህርት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የሚገባውን ቦታ እንዳያገኝ ተደርጎ ቆይቷል።

"ደማችሁ ከደማችን አንድ አይደለም" በማለት በተለያዩ ቦታዎች በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለዘመናት በኖሩበት አካባቢ አትታወቁም ተባሉ፤ ተገደሉ፣ ቤታቸው ተቃጠለ፣ ንብረታቸው ተዘረፈ፣ ከቀያቸው ተፈናቀሉ፣ በአገራቸው ውስጥ ስደተኞች ሆኑ። ለዚህ የጎሰኝነት ችግር ሰለባ የሆኑት አካባቢዎች በአብዛኛው ኦሮሚያን፣ ጋምቤላን፣ ሶማሌን፣ ደቡብን፣ ቤኒሻንጉል-ጉምዝን፣ ወላይታን፣ ጉጂን፣ ጌዴዖንና አማራን የሚሸፍን ሲሆን፣ ሰሞኑን ደግሞ በሰሜን ሸዋ በካራቆሬ፣ በአጣዬ፣ በማጀቴ፣ በከሚሴ፣ በአጣዬ በማጀቴና በሌሎችም ቦታዎች ክቡር የሰው ልጅ ሕይወት ጠፍቷል፣ ብዙዎች አካለጎደሎ ሆነዋል፣ ንብረታቸው ተዘርፏል፣ ተቃጥሏል፣ ቀሪው ሕዝብም በስጋት እየኖረ ይገኛል። በሀገሪቱ ውስጥ የተፈናቃዮች ቁጥር በሚሊየኖች

የሚቆጠር መሆኑን ድርጅቶችና የመገናኛ ብዙሃን ቢዘግቡም በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ችግሩን መፍታት አልቻለም።

የተጀመረው የለውጥ ሂደት ኢትዮጵያዊነትን ለሚያራምደው ወገን ደስታ ሲፈጥርለት ጎሰኝነትን በሚያቀነቅነውና በዚያም ሳቢያ ያልለፋበትን እያጋበሰ ኑሮውን ላደላደለው ወገን ደግሞ ድንጋጤ ወረደበት። ሰኔ አሥራ ስድስት ቀን 2010 ዓ. ም. በጉጉት የጠበቋቸው የለውጥ አራማጅ መሪ ሕዝቡን ያስደሰተ ንግግራቸን ጨርሰው ወደ መቀመጫቸው ሲመለሱ የቦንብ ፍንዳታ ተከሰተ። ያ በቅርብ ርቀት ታልሞ የፈነዳ ቦምብ ዒላማውን አልመታም። ይሁን እንጂ ተስፋ የፈነጠቀውን ለውጥ ለማጨለም ሤራውን የሸረቡት በሥልጣን ላይ ካለው ዘረኛ መዋቅር ጋር የተጋመዱ መሆናቸው ለውጡ ውስብስብ ሊሆን መቻሉን አመላከተ።

በኢትዮጵያዊነትና በጎሰኝነት መካከል የተፈጠረው ፍጥጫ በተለያዩ መንገዶች ቀጥሎ እጅግ የከፋውና አዲስ አበባንና አገሪቱን ብቻ ሳይሆን የዓለምን ሕዝብ ጭምር ያስደነገጠ የጎሰኝነትና የጥላቻ ብትር ቡራዩ በሚኖሩ ዜጎች ላይ ተሰንዝሮ፣ ዜጎች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገደሉ፣ ሴቶች ተደፈሩ፣ ንብረት ተዘረፈ፣ ተቃጠለ፣ ህፃናትም ጭምር የጥቃቱ ሰለባ ሆኑ። የፀጥታ ኃይሉ በሥፍራው ቢገኝም "አልታዘዝኩም" በማለት ሰንካላ ምክንያት የሕዝብን ሕይወት ለማትረፍ ሲንቀሳቀስና ወንጀለኞችን ሲቆጣጠር አልታየም። ወጣት የተጠቂ ወገኖች ለበቀል ቢነሱም፣ ሽማግሌዎች እርጥብ ሣር ይዘው ተንበርክከው ልጆቻቸው ክፉትን በክፉት እንዳይመልሱ ተማጸኗቸው። ኢትዮጵያዊነትና ጨዋ ባህል አሸነፈ፣ ሰላምም ሰፈነ። በለገጣፎም አካባቢ የመንግሥት አካላት ባደረጉት የቤት ማፍረስ ዘመቻ በርካታ ነዋሪዎች ከቤታቸው ተፈናቅለው መጠለያ ውስጥ ገቡ። እነዚህ ሁሉ ጎሣን መሠረት ያደረጉ የሰው ልጅ ስቃይና መከራዎች ሊቆሙ ሲገባቸው እንደቀጠሉ መሆናቸው እጅግ አሳሳቢ ነው።

የአዲስ አበባ ችግር ደግሞ አገረሸ። ከልዩ ጥቅም ይገባኛል ጥያቄ አልፎ የባለቤትነት ጥያቄ በማኅበራዊ ሚዲያው ይናፈስ ጀመረ። የአዲስ አበባ መስተዳድር የኮንዶሚኒየም ዕጣ የደረሳቸውን ነዋሪዎች ይፋ አደረገ። የመኖሪያ ሠፈሮቹ የተገነቡት ከአዲስ አበባ አጎራባች በሆኑ የኦሮሚያ መሬት ላይ በመሆኑ ቤቶቹ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሊሰጡ አይገባቸውም በሚል ተቃውሞው ተቀጣጠለ። ተቃውሞው ግን በአዲስ አበባና አካባቢው ብቻ አላቆመም። በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የተቃውሞ ሰልፎች ተካሄዱ።

የመኖሪያ ቤት ዕጣ መውጣቱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት መግለጫዎች ተከታተሉ።

የሕግ የበላይነት አለ በሚባልበት አገር ማንም ዜጋ በቡድን እንቅስቃሴና ብይን ሕይወቱንና ንብረቱን፣ የአካል ደህንነቱንና የመዘዋወር መብቱን፣ በአገሩ ውስጥ በመረጠው ሥፍራ ንብረት አፍርቶ የመኖር ነፃነቱን ሊያጣ አይገባውም። አንድ ዜጋ በዜግነቱ የሚገባውን መብት ሁሉ ሳይዛነፍ ተጠብቆለት በመረጠው ሥፍራ የመኖር መብት አለው። የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጣስ፣ መገደብና መከልከል የዴሞክራሲያዊ አገር ሕግ መጣስ ብቻ ሳይሆን የዓለም ሃገራት የተስማሙበትን ሁለንተናዊ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የያዘውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ዓለም አቀፍ ሰነድ መጣስና ዓለምአቀፋዊ ወንጀል መፈጸምም ነው።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ውስጥ የሰፈነውን የጎሣ ጥላቻን መሠረት ያደረገ እንቅስቃሴ ለማስቆምና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግርን ሂደት ለማሳካት የአንድ አካል ጥረት ብቻ በቂ አይደለም። ይህ ታሪካዊ አጋጣሚ እንደ 1966ቱ፣ 1983ቱና 1997ቱ አጋጣሚዎች አሁንም እንዳይተኳጎል፣ በመጀመሪያ ደረጃ ዜጎች ቀጥሎም ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ የለውጡ ሂደት እንዳይቀለበስ ማድረግ ያስፈልጋል። እናፍታታው፡-

1. **መንግሥት፡-** እያንዳንዱ ሀገር በሀገሪቷ የጂኦግራፊያዊ ክልል ውስጥ የሚኖረውን ሕዝብ የሚያስተዳድር መንግሥት አለው። ሕዝቡ እንደ ፈረንሳይ ተመሳሳይ፣ አለያም እንደ አሜሪካና ሌሎች ሀገራት በቋንቋው፣ በምንጩና በባህሉም የተለያየ ሊሆን ይችላል። ሕዝብን የሚያስተዳድር መንግሥት ደግሞ ሕግ አውጭ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ አካላት ይኖሩታል። በሕጉ መሠረት የሀገሪቷ ዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን የሚያረጋግጠውም መንግሥት ነው። የመንግሥት የመጀመሪያ ተግባር ሕዝብ በሰላም እንዲኖር ማድረግ ሲሆን፣ የሕግ የበላይነትን ማስከበር፣ የግለሰብንና የቡድን መብትን ማስከበርም የመንግሥት ግዴታ ነው።

   ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች የሚጣሱባት፣ ሕዝብ በሰላም ውሎ ማደርን የሚናፍቅባት፣ ሕዝብ በረሃብ አለንጋ መገረፍ የተለመደባት፣ አጥንትና ቆዳቸው የተጣበቀ ሕፃናት የሚታዩባት፣... ወ.ዘ.ተ መሆኗ ሳያንሳት፣ በዘረኝነት አረንቋ ውስጥ ገብታ እንድትማስን የተፈረደባት፣ መንግሥት የሰዎችን በሕግ ፊት እኩል መሆን የሚያረጋግጥ ኃይል ሳይሆን የቡድኖችን ከሕግ በላይ መሆንና ሰብዓዊ መብትን የሚጥስ አካል ሆኖ ነው

ኢ.ህአዴግ-መራሹ መንግሥት የኖረው። በመሆኑም ኢትዮጵያ በብጥብጥና በአመጽ የተዋከበች አገር ሆና ኖረች።

ለውጥ የግድ ነውና ኢ-ዴሞክራሲያዊነት በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ለውጡን የሚመሩ ሰዎች ብቅ ብለው በርካታ ለውጦች እየተካሄዱ ቢሆንም ለውጡ ገና እስከታችኛው እርከን አልዘለቀም። ከሕግ በላይ ሆነው ሕዝብንና ሀገርን ሲበድሉ የኖሩ ሁሉ ለፍርድ አልቀረቡም። በአንዳንድ ቦታዎች እነዚያው ሰዎች የለውጥ አራማጅ ተብለው በሥልጣን ላይ ስለሚገኙ የለውጥ ሂደቱን በማስቀጠልና በማጨናገፍ መካከል የሚደረገው ትግል እንዲወሳሰብ ሆኗል። በመሆኑም የሕግ የበላይነትን ጥሰት ማስቀረት አልተቻለም። መንግሥት የሕግ የበላይነትን ማስከበር የማይችልባቸው ሁኔታዎች በርካታ ናቸው። ሰብዓዊ መብት ሲጣስ፣ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ስደተኛ ሲሆኑ፣ ሕፃናት ሲንገላቱና እናቶች በልጆቻቸው መራብና መጎሳቆል የተነሳ ኀሊናቸው ሲጎዳና ሲሳቀቁ... መንግሥት በዝምታ መመልከቱ አግባብ አይደለም። ለውጡን ለመግፋትና ከዳር ለማድረስ ይቻል ዘንድ መንግሥት የሕግ የበላይነት የማስከበርን መሠረታዊ ኃላፊነት በብቃት መወጣት ይጠበቅበታል። ሀገራችንን ወደ ተሻለ ሥርዓት ለመለወጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ስላሉ፣ መንግሥት ከተፎካካሪ ኃይሎች ጋር በመምከር የሚፈለገውን ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

2. **ሕዝብ፡-** የሰው ልጆች፣ በተጻፈም ይሁን ባልተጻፈ የሕግ ጥላ ሥር ተከልለው የሚኖሩ በመሆኑ፣ ሕጉ የሚፈቅድላቸውን መብትና የጣለባቸውን ግዴታ ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕግ ተገዥና ለሀገራዊ ሉዓላዊነት ያለውን ክብር በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ከመሆኑም በላይ ሀገራዊ አንድነት ሲደፈር መስዋዕትነት ከመክፈል ወደኋላ የማይል፣ ጎሣን ሳይሆን ሀገርን የሚያስቀድም ሕዝብ መሆኑን በተደጋጋሚ አሳይቷል። ይሁን እንጂ ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያደረበት ሕዝብ በመሆኑ በሕግ የተረጋገጠለት መብቱ በተደጋጋሚ ሲደፈር ሁሉን ነገር ለፈጣሪው ሰጥቶ በዝምታ ሲያልፍም ተስተውሏል። ዝምታ አያዋጣም፤ ፀጥ ባለ ሌሊት የቅጠል ኮሽታ ጎልቶ እንደሚሰማ ሁሉ፣ ፀጥ ባለ ሕዝብ መሃል የጥቂት ትዕቢተኞች፣ ክልልተኞች፣ ጎጠኞችና እንጭጮች ድምፅ አገርን እያናወጠ የሚሰማበት ሁኔታን ፈጥሯል። የሕግ የበላይነት ሲጣስ በዝምታ ማለፍ ስብዕናን ከማዋረድ አልፎ ሀገርን ማጣት ሊያስከትል ስለሚችል በሀገራችን ጉዳይ ላይ በንቃት መሳተፍ ያስፈልጋል፣ ይጠበቅብናልም። የዘረኝነት አስተሳሰብ ነግሦ ኢትዮጵያዊነት ማፈሪያ ከሆነበት ሥርዓት ለመውጣት የፈነጠቀው የተስፋ ብርሃን

እንዳይጨልም፤ ሃሳብን በግልጽ ማሰማት፣ ፍላጎትን ከነምክንያቶቹ መግለጽ፣ ተሰሚነት ሲታጣ ደግሞ በሠላማዊ መንገድ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ (ሰላማዊ ሰልፍ፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን መጥራት፣ የሥራ ማቆም አድማም መጥራት…ወዘተ)፣ የሃሳብ ፍጭት በሰላማዊ መንገድ እንዲቀጥል የበኩልን አስተዋጽዖ ማበርከት ያስፈልጋል። ከሕግ በላይ የዋሉ የመሰላቸው ሕገወጦችን በሕግ እንዲጠየቁ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማሰማት ያስፈልጋል። ለዚህም በየትኛውም የዓለም ጠርዝ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተጀመረው ለውጥ ግቡን እንዲመታ የሕዝቡን ድምፅ በከፍተኛ ደረጃ ማስተጋባት ይጠበቅባቸዋል።

በሀገራችን ውስጥ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘይቤዎች በመቻቻልና በመፈቃቀር የዜጎች ትስስር ትውልድ ተሻጋሪ ሆኖ ኖሯል። ይህንን ባህላዊና ሀገር-በቀል እሴት አጠንክሮ ማስቀጠል በሀገር ውስጥ ጠብና ግጭት አስወግዶ ወደ ከፋ ሁኔታ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዞ እንዳይመጣ በማድረግ ሰላምን ማስፈን ይቻላል። ከእርስበርስ ግጭት፣ ከፀብ፣ ከቂም በቀል ማንም ተጠቃሚ አይሆንም። ሰላምና መረጋጋትን ዛሬ በሁላችንም በተደራጀ፣ በተጠናከረና ቀጣይነት ባለው ትግል ማስፈን ካልቻልን እጅግ አስከፊ የሆነ የእርስበርስ መጠፋፋትና ለትውልድ የሚተርፍ ቂምበቀልን የምናወርስ ስለሚሆን አንድነትን፣ እኩልነትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን ለማውረስ ሳንታክት ጠንክረን መሥራት ይኖርብናል። ስለሆነም ከጎሣ ፖለቲካ የፀዳች ሀገር እውን ለማድረግ ሕዝብ ከራሱ የጎሣ አስተሳሰብ መውጣትና ሀገራዊ አንድነትን ለማምጣት የሚጠቅሙ ሃሳቦችን ማቀንቀን እንዳለበት እንዲሁም አክራሪ ጎሠኞችን በጽኑ መቃወም እንደሚገባው ልናሰምርበት እንወዳለን።

3. **የፀጥታ ኃይሎች፡-** የፀጥታ ኃይሎች ሕግ አስከባሪዎች እንደመሆናቸው መጠን ማንኛውም አካል ከሕግ በላይ ሲሆን በዝምታ መመልከት የለባቸውም። ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይንም እንቅስቃሴ ጋር ሳይወግኑ፣ የሀገራዊም ሆነ የክልላዊ መንግሥት ተቋሞች ስለሆኑ ብቻ፣ የሕዝብን ሰላም፣ ጸጥታና መረጋጋት ማረጋገጥ፣ ማስጠበቅ ግዴታቸው ነው። ሕግና ሥርዓት ሲጣስ፣ የዜጎች ሰብዓዊ መብታቸው ሲረገጥ፣ የሰው ልጅ ኢ-ሰብዓዊ በደል ሲደርስበት፣ ሕፃናት ሲሰቃዩ፣ ሴቶች ሲደፈሩ፣ የሕዝብ ንብረት ሲወድም… ወ.ዘ.ተ እየተመለከቱ "ትዕዛዝ አልተሰጠኝም" በማለት በዝምታ ማለፍ፣ የቡድን ፍርድ ሲፈጸም "ትዕዛዝ" በመጠበቅ ዝም ብሎ ማየት አግባብ ካለመሆኑም በላይ በዓለም አቀፍ ሕግም አስጠያቂ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም የፀጥታ ኃይሎች የሕግ የበላይነትን ማስከበርና ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን ተቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑን ላፍታም ሳይዘነጉ ሀገራዊ ግዴታቸውን ሙያዊ ብቃትን

በተላበሰ መልኩ መወጣት ከምንጊዜውም በላይ ወቅቱ አሁን መሆኑን አጠንክረን ለማሳሰብ እንወዳለን።

4. **የፖለቲካ ፓርቲዎች፡-** ዴሞክራሲ በሌለበት ሀገር የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊኖሩ ይችላሉ፣ አምባገነናዊ ገዥ ፓርቲዎች ወይንም ድንግዝግዝ ያላቸው "ተቃዋሚዎች" ሊሆኑ ይችላሉ። ሕይወት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በሌሉበት ሀገር ግን ዴሞክራሲ አለ ማለት አይቻልም። ፓርቲዎች የፖለቲካ አማራጮችን ማቅረብና በሕዝብ ውይይት እንዲዳብሩ በማድረግ በተግባሮቻቸውና በዓላማቸው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና የፖለቲካ ሥርዓቱ እንዲጠነክር አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት፣ ለሥልጣን በመወዳደር የዴሞክራሲ ብዙሃንነትን የሚገልጽ ሥርዓት እንዲጠነክርም ያደርጋሉ። በምርጫ ወቅት ተሸናፊ ቢሆኑም እንኳን አሸናፊ ፓርቲዎች ላይ ጠንካራና አዎንታዊ ትችቶችን በመሰንዘር የመረጣቸውን ሕዝብ ፍላጎት እንዲያከብሩ ጫና ማሳደር ሲችሉ ለቀጣዩ ጊዜ የተሻለ አማራጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያሳያሉ። ዴሞክራሲያዊ አሠራሮች ሲጣሱም ጥሰቶቹን በመቃወም ከሕዝብ ጎን ይቆማሉ።
ፓርቲዎች ዴሞክራሲ ባልደረጀባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ሕዝብ ለዴሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል ማቀናጀትና መምራት፣ የሕዝቡ አንደበት ሆነው ድምጹን ማሰማትና የሰላማዊ ትግሉን አቅጣጫ መምራት ይኖርባቸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም እንኳን የይስሙላ ምርጫዎች ሲደረጉ ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም አሸንፌአለሁ የሚለው ፓርቲ ዴሞክራሲን ከማጠናከር ይልቅ ሲያቀጭጭና የአንድ ፓርቲ የበላይነትን ሲያሰፍን ኖሯል። ኢትዮጵያ ባለችበት ሁኔታ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ተሳትፎ መድረክ የተዘጋጀ ቢመስልም የዴሞክራሲ ተቋማት ብቁ አለመሆን ሂደቱን ሲያጓትተው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ወቅቱ የሚጠይቀውን የመሪነት ሚና መጫወት በሚችሉበት ቁመና ላይ አለመገኘታቸው አሳሳቢ ነው።

የጎሣ ፖለቲካው እየቀደመ ጎሠኖችም ሀገራዊ አጀንዳውን ለመሸፈን ሲጣደፉ፣ ሀገራዊ ፓርቲዎች አጀንዳቸው ለሀገር ኅልውናና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አበክረው በመግለጽ ሕዝቡ አገርን ከመፍረስ አደጋ እንዲታደግ ለማድረግ የሚጠበቅባቸውን የአመራር ሚና በሃላፊነት መንፈስ መጫወት ይገባቸዋል። በተጨማሪም የተዛባውን ሁኔታ ማስተካከልና ያልገባውንም የኅብረተሰብ ክፍል ማስተማር ይገባቸዋል። ፓርቲዎች የያዙት ዓላማ ምንም ይሁን ምን የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አማራጭ አስተሳሰቦቻቸውን በግልጽ በማሳየት "ከእናውቅልሃለን" ባዮችና ከአምባገነናዊ ሥርዓት ለማላቀቅ የሚያደርጉትን ትግል አጠናክረው መቀጠል

ይገባቸዋል። ይህ ወሳኝነት ያለው ሀገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በአንድ ወይም በጥቂት ድርጅቶች ትግል ብቻ ሊከናወን እንደማይችል በመረዳት ከሌሎች በርካታ ፓርቲዎች ጋር በመተባበር የለውጡን ሂደት በማጠናከር፣ ከግቡ ማድረስ ይጠበቅባቸዋል እንላለን።

5. **የሲቪል ማኅበራት፡-** የሲቪል ማኅበራት ሕዝቡን በማስተማር ተግባር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ የሚታወቅ ነው። ሀገራችን ውስጥ አሁን ባለው ሁኔታም የሲቪክ ማኅበራት ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋጽዖ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ የዴሞክራሲያዊ አሠራር እንዲጎለብት ሕዝቡን የማስተማር ኃላፊነታቸውን በስፋትና በጥልቀት መወጣት አለባቸው። በተጨማሪም የሕግ የበላይነት ሲጣስ በዝምታ መመልከት ሳይሆን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕዝቡን የማስተማር፣ የመቀስቀስ፣ ለመብቱ እንዲታገል የመነትነት ታሪካዊ ተግባራቸውን በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥሉ እናሳስባለን።
6. **የመንግሥትና የግል የመገናኛ ብዙሃን፡-** የመገናኛ ብዙሃን ለዴሞክራሲ ዕድገትና ለሀገር ግንባታ የሚሠሩ እንጂ የድርጅቶች ተቀጽላ ሆነው የድርጅቶችን አቋም የሚደግፉና የሚያስተጋቡ ተቋማት አይደሉም። ለዚህም ብቃትን በተላበሰ መልኩ ከማንም ድርጅት (መንግሥትን ጨምሮ) ሳይወግኑ ሚዛናዊ መረጃዎችን ለሕዝብ ማድረስ ሙያዊ ግዴታቸው በመሆኑ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። አንድ የመገናኛ ብዙሃን፣ በሕዝብ መካከል አንድነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን የሚያጎለብት ሳይሆን ጎሠኝነትን የሚያናፍስ፣ ጥላቻን የሚያራምድና ኢትዮጵያን የሚያፈርሱ፣ ሕዝቡን የሚያጋጩ ጥሪዎችንና ቅስቀሳዎችን ደጋግሞ የሚያሠራጭ ሆኖ ከተገኘ፣ ተቋሙ በሕግ ሊጠየቅ ይገባዋል። የመገናኛ ብዙሃን ባልደረቦች በሕዝብ ላይ በደል ሲፈጸምና ሕግ ሲጣስ፣ ያለማጋነን ሃቁን እንዲያቀርቡ ሙያዊ ግዴታቸው የሚያስገድዳቸው መሆኑን እያስገነዘብን፣ እንደ ስማቸው ከሕዝብ የሚወግኑ መሆን እንደሚገባቸው ልናሳስባቸው እንወዳለን።
7. **የዓለም መንግሥታት ተቋማትና የዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ፦** የኢትዮጵያ ጉዳይ በዋናነት የኢትዮጵያውያን ነው። ያም ሆኖ፣ ሀገራት የዓለም መንግሥታት ድርጅት ሕግ በሚፈቅደው መልኩ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጠሩ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት ትኩረት በመስጠት የዜጎች መብቶች እንዲከበሩ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማሰማት ይጠበቅባቸዋል። የዓለምአቀፍ ድርጅቶችም ቢሆኑ ነገሮችን በዝምታ መመልከታቸው ትክክል ስለማይሆን ከኢትዮጵይ ሕዝብ ጎን በመቆም ስቆቃ እንዳይፈጸምበት የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ እናሳስባለን።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከጥንስሱ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነት፣ በሕዝቡ እኩልነት ላይ ለተመሠረተ ሀገራዊ አንድነቱ የታገለ እንደመሆኑ፣ አሁንም በነዚህ መሠረታዊ መርሆች በመመራት ከላይ የተጠቀሱትን ዴሞክራሲያዊ አቋሞች እውን ለማድረግና እኒህን የሃገሪቱንና የሕዝቧን መሠረታዊ መብቶች የሚቀናቀን አመለካከትንና አካል ያለማወላወል እንደሚታገል በድጋሚ ቃል ይገባል።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኖራለች!